# አድልዎ ያለመፈጸም ማስጠንቀቂያ

Johns Hopkins የጤና ክብካቤ አቅራቢዎች እና ሁሉም የJohns Hopkins Medicine ሠራተኞች በስራ ያሉትን ሁሉንም የፌደራል የሲቪል መብት ህጎች የሚያከብሩ ሲሆን በዘር፣ በቀለም፣ በብሔር፣ በትውልድ ሐገር፣ በእድሜ፣ በቋንቋ፣ በአካላዊ ወይም አእምሯዊ አካል ጉዳተኝነት፣ በኃይማኖት፣ በጾታ፣ በወሲባዊ ዝንባሌ እና በስርዓተ ጾታ ማንነት ወይም አገላለጽ ላይ ተመስርተው ሠዎች ላይ አድልዎ አይፈጽሙም፣ አይለዩም ወይም አያስተናግዱም። ይህን ማስጠንቀቂያ የሚከተሉት ድርጅቶች (በጥቅሉ "Johns Hopkins Medicine Entities") ተብለው የሚገለጹት በአገልግሎት መስጫ ቦታቸው ለህዝቡ የክብካቤ አገልግሎት የሚሠጡትን ሁሉንም የJohns Hopkins የጤና ክብካቤ አቅራቢዎችን እና በማስጠንቀቂያው ውስጥ የተጠቀሱትን ጨምሮ የJohns Hopkins Medicine ሠራተኞችን ያካትታሉ።

Johns Hopkins Medicine Entities:

- የአካል ጉዳት ላለባቸው ሠዎች ከኛ ጋር በጥሩ ሁኔታ መግባባት እንዲችሉ ነጻ ድጋፎችና አገልግሎቶችን ለምሳሌ ብቃት ያላቸው የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚዎችን፣ የጽሁፍ መረጃዎችን በሌሎች ቅርጾች (ከፍ ባለ ህትመት፣ በድምጽ፣ ተደራሽ በሆኑ ኤሌክትሮኒክ ቅርጾች፣ ሌሎች ቅርጾች) የሚሠጡ ሲሆን
- የመጀመሪያ ቋንቋቸው እንግሊዘኛ ላልሆነ ሠዎች ነጻ የቋንቋ አገልግሎቶችን ለምሳሌ ብቃት ያላቸው አስተርጓሚዎች እና በሌሎች ቋንቋዎች የተጻፉ መረጃዎችን ይሠጣሉ

እነዚህን አገልግሎቶች ማግኘት የሚፈልጉ ከሆነ፣ እርስዎ ወይም ተወካይዎ ለእርስዋ የህክምና ቡድን አንድ አባል ለምሳሌ ለነርስ፣ ለከፍተኛ የህክምና ባለሙያ ወይም ለሐኪም ሊያሳውቅ ይችላል።

እርስዎ ወይም ተወካይዎ የህክምና አገልግሎቶችን እየሠጠዎት ያለው የJohns Hopkins Entity እነዚህን አገልግሎቶች መስጠት አልቻለም ወይም በዘር፣ በቀለም፣ በትውልድ ሀገር፣ በእድሜ፣ በአካል ጉዳተኝነት ወይሞ በጾታ ላይ ተመስርቶ በሌላ መልኩ አድልዎ ፈጽሟል ብላችሁ ካመናችሁ፣ መደበኛ አቤቱታ ወይም ቅሬታ ማቅረብ ለመጀመር እርስዎ ወይም ተወካይዎ ከታካሚ ግንኙነት ጽ/ቤት ጋር መገናኘት ትችላላችሁ።
ቅሬታዎን ለማቅረብ ድጋፍ ማግኘት የሚፈልጉ ከሆነ፣ ከታካሚ ግንኙነት ጽ/ቤት (Patient Relations Office) ወይም በእርስዎ Johns Hopkins Medicine (JHM) Entity ውስጥ ካለ አግባብነት ካለው አንድ ተጠሪ ድጋፍ ሊያገኙ ይችላሉ። የታካሚ ቅሬታ እና አቤቱታ ለማቅረብ የግንኙነት መረጃ ለማግኘት የJHM Patient Rights and Responsibility (የታካሚ መብቶች እና ኃላፊነት) ድረገጽን ይመልከቱ።

በተጨማሪም የሲቪል መብት ቅሬታን ለዩኤስ የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ, የሲቪል መብቶች ቢሮ (U.S. Department of Health and Human Services, Office for Civil Rights) በፖስታ ወይም በሚከተለው አድራሻ ሊያቀርቡ ይችላሉ:

U.S. Department of Health and
Human Services 200 Independence
Avenue, SW Room 509F, HHH
Building Washington,
D.C. 20201
1-800-368-1019, 800-537-7697 (TDD)
የቅሬታ ማቅረቢያ ቅጾችን ከዚህ ድረገጽ ማግኘት ይቻላል http://www.hhs.gov/ocr/office/file/index.html

የካቲት 28፣ 2022